# የእምነትና የሞራል ግዴታ

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**
nigatuasteraye@gmail.com

**ሕዳር ፳፻፫ ዓ.ም.**

*በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ በመንግስትና በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያሉ ሰዎች ስለየሚያደርጓቸው ተደጋጋሚ በደሎች ዘወትር የሚነገሩትና የሚጻፉት ነገሮች እንደሚያስለቱ የታወቀ ነገር ነው። በሆንም ቀድሞ በባህላችን ሲደረጉ አስገራሚና አስደንጋጭ የነበሩ ስህተቶች ተደጋግመው በመደረጋቸው እየተለመዱ፤ ስለነሱም በተደጋጋሚ የሚነገሩትና የሚጻፉት አሰልቺተውናል። ቢሆንም፤ ሰልችተን ርግፍ አርገን ከተውናቸው፤ ስህተተ ፈጻሚዎች በስህተታቸው ስለሚቀጥሉና ስህተቶችም የባህል ውርስ ሆኖነው እንዳሸገሩ፤ ስህተተኞችም ከስህተታቸው እንዲገቱ ለማሳሰብ፤ የእምነትና የሞራል ግዴታ በሚል ርእስ ይህችን ጠማር አዘጋጀሁ።*

## <u>መግቢያ</u>

ከጥንት ጀምሮ ሰው የሚወቀስበትና የሚከሰስበትን በደልና ኃጢአት ከመፈጸም ራሳቸውን ለማግለል ከራሳቸው ጋራ እየታገሉ፤ በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊው መስመር የሞራልና የእምነት ምስክርነት በመስጠት ድርሻቸውን፤ ግዴታቸውንና ሃለፊነትን እየተወጡ ያለፉ ሰዎች ዛሬ ባለንበት ዘመን ካሉት ይል ቁጥራቸው ይበዛ ነበር። ሲደረግ ባዩትና በሰሙት ኃጢአትና በደል የሚሰጡትን ምስክርነት በጥቅምና በከንቱ ውዳሴ አልገቱም። መታሰርና መንገላታት ይገጥመናል ብለው ሳይፈሩ፤ በቅኔያቸውና በንግግራቸው የመሰከሩ ነቢይ (ነብያት)፤ (ሐዋርያ፥ ሐዋርያት)፤ (ሰምእ፥ ሰማእት፥ ሰማእታት) በየ ህብረተ ሰቡ እንደነበሩ በኛም ዘንድ ነበሩ።

ከኦሪቱ ናታንን ከሐዲሱ ደግሞ እስጢፋኖስን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። እስጢፋኖስ የከበበውን ኃይል ሳይፈራ፤ ከኔ በተሻለ የሚሰሙ ሐዋርያት እያሉ፤ እኔ ምን አገባኝ ሳይል፤ ራሳቸው እውነቱን ስተው ህዝቡን በማሳሳት ላይ ያሉትን ሰዎች “እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮቻችሁ ያልተገረዘ” (የሐዋ ፯፥ ፶፩)፤ እያለ በመናገሩ ነቢይ (ተናጋሪ) ወይም ሰማእት ተባለ።

የናታን ትንቢታዊ አቀራረብ፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሊቃውንት አበው ብዙ ጊዜ የተጠቀሙበት ከቅኔያችን ጋራ ተመሳሳይ ስለሆነ በትኩረት ብንመለከተው በቤተ ክህነታችን የነበረውን ለማወቅና ዛሬ እምን ላይ እንዳለን ለመገመት የሚረዳን ይመስለኛል። ናታን በነበረበት ከተማ የተፈጸመውን ግፍና በደል በሰምና ወርቅ ቅኔ ያገለጠ ነቢይ (ተናጋሪ) ነበር። ንጉሥ ዳዊት ስልጣኑን በመጠቀም የኦርዮንን ሚስት፥ ቤርሳቤህን ከደፈረ በኋላ፡ ነገሩን ለመሸፈን ሲል፤ የቤርሳቤህን ባል ኦርዮንን በእጅ አዙር አስገደለው። በዚህ ጊዜ ናታን በግላዊ ጥቅማ ጥቅም ሳይደለል፤ ባለ ስልጣኑንም

ሳይፈራ፤ የሚከተለውን ሰምና ወርቅ ቅኔ በመጠቀም የተደራረበ በደልና ኃጢአት የፈጸመውን ንጉሥ ዳዊትን አጋለጠው።

የተደፈረችውን የኦርዮንን ሚስት ቤርሳቤህን፤ ከአንድ ድሀ ተነጥቃ በተበላች በግ መስሎ አቀረባት (፪ኛ ሳሙ. ፲፪፡፩-፭)። በግፍ የተነጠቀውንና የተገደለውን ባሏን (ኦርዮን) በበጓ ባለቤት መስሎ አቀረበው። በተፈጻጻሚዎች ኃጢአቶች፤ በዝሙት፤ በስርቆት፤ በነፍሰ ገዳይነትና በፍርድ አጉዳይነት ዳዊትን ጠልፎ የከተተ፤ አርቆ የሚያሳይ ትንቢታዊ ቅኔ አዘጋጀና ለራሱ ለዳዊት አቀረበለት።

ራሱን ከራሱ ሕሊና የሰረቀው ዳዊት፤ መስታወት ሆኖ በቀረበለት ቅኔ ስለ ሌላ ሰው የሚገልጽ መስሎት "ይህን ያደረገ ሰው መሞት የሚገባ ሰው ነው"(፭) ብሎ ፈረደ። ናታን ግን "ያ ሰው አንተው ራስህ ነህ"(፯) አለው። ዳዊት በሰው ላይ የፈረደውን ፍርድ፤ ባለ ቅኔው ናታን ዳዊትን አከናነበው። ማለት፦ የፈረደከው ፍርድ ትክክል ቢሆንም፤ ፍርዱ ሊፈጸም የሚችለው ራስህ የበደሉ ፈጻሚ መራራዋን የፍርድ ጽዋ ስትጠጣት ነውና፤ ራስህ ጠጣት አለው። (፲፩ እና ፲፪) ምዕራፎችን ይመልከቱ።

ከዳዊት ጋራ ተጣምሮ የቀረበው <u>አክአብ</u> የተባለው ሰው ነው። ይህ ሰው ደካማውን በማታለል፤ እምቢ ያለውን በእጅ አዙር በማስገደልና አስገደዶ በመቀማት እጅግ የሰለጠነች ከሱ የክፋች ጨካኝና ስግብግብ ሚስት ነበረችው። (ቀ. ነ.ምዕ ፳፡፲፬-፳፯)። በራሱና በሚስቱ ስግብግብ ባህርይ እየተመራ የድሆችን የነ ናቡቴን ርስት መሬት እየነጠቀ ለራሱ እኩይ ተግባር ስሜት ማርኪያ በማድረጉ፤ ኤልያስ የተባለውን ነቢይ እግዚአብሔር አስነሳ።ኤልያስም "በእግዚአብሄር ፊት ክፉ ለማድረግ ራስህን ሸጠሀል፤ ክፉ ነገር አመጣብሀለሁ"(፳) በማለት፤ <u>ሞራላቸውንና ሕሊናቸውን ለገንዘብ ሸጠው ይህን መሳይ ግፍ በሚሰሩት ሰዎች ሁሉ ላይ በመጨረሻ የሚመጣባቸውን ቅጣት ነገረው</u>።

በቤተ ክህነታችንም ይህንን የመሳሰሉ ቅኔዎች በማቅራብ የሚገስጹና ወደ ንስሀ የሚመልሱ ሊቃውንት ነበሩን። ቅኔዎቻችን በመጀመሪያ ክፍሎቻቸው በዕለቱ የሚታወሰውን በቃሉና በደሙ መስክሮ ያለፈውን ሰማእት ወይም ነቢይ ካስታወሰን በኋላ፤ "አሰረ ንጉሥ""" እና "እስመ ለዓለም" በሚባሉ ክፍሎች በዘመናችን ባካባቢያችን ያሉ መሪዎች የሚፈጸሙት ስህተቶችና በጎ ነገሮች የምናጸባርቅባቸው ክፍሎች ናቸው።

ለምሳሌ የምንጠቅሳቸው እንደ እነ ሊቀ ካህናት ወልደ ዮና የመሳሰሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አበው ነበሩ። እኒህ ሊቅ በዘመናቸው በገፊና በተገፊ መካከል የሚፈጸመውን ግፍና በደል ተመለከቱ። በዝሙት በነፍሰ ገዳይነትና በፍርድ አዛቢነት ላይ ያሉትን በዳዊት መሰለው፤ ባለ ርስቱን ባለ አገሩን ካገሩ ከርስቱ እያፈናቀሉ በማሰቃየት ላይ ያሉትን ደግሞ በክአብ መሰለው የዘመኑን ብሶት ለመግለጸ የሚከለውን መወድስ ቅኔ ተቀኙ።

"ለገጸ ገፋኢ ትሰፍህ መንጠላዕተ ርትዕ፤ መርዓዊ ተውላጥ ክርስቶስ ግፉዕ እንዘ እራቁ።
ወእንዘ ኢርቱዕ ለሰብእ ለቤተ ምኩናኒከ ንድቁ።
ዳዊት ወአክአብ፤ እለ ትእዛዘከ መዝገበ ሰረቁ።
ውስተ ግበ ጌጋይ አመ ወድቁ፤ ለዳዊ ትቴክዝ ወለአክአብ ታስቆቁ።
አንተሰ ወዳዊት እመ ትታረቁ።
ዳዊት ወያርዮ ነገረ ቤርሳቤህ ኢያህለቁ።
ባህቱ ፍዳሆሙ ልቅህ ኢፈደይክሙ በሕቁ።
ለዳዊት በከመ ግፉዕ ወለያርዮን በከመ ጽድቁ"

ድሮ እንደ አክአብ አልጠግብ ባይ ስግብግቦች፤ እንደ ዳዊት አመንዝራዎችና ነፍሰ ገዳዮዮች ብቅ በሚሉበት ዘመን "የዛሬው ባለ ቅኔ ምን ብሎ ተቀኘ?" ብለው በመጠየቅ የራሳቸውን ስሜት ለመቆጣጠር የሚታገሉ ሰዎች ነበሩ። ዘመኑን ዘመን እየተካው፡ ትውልዱን ትውልድ እየዋጠው ሲመጣ፡ የቅኔወችን ቦታ ጋዜጠኞች እየተኩ፤ የቅኔው አገልግሎት እየተረሳ መጣ።

ከኦሪቱ ጀምሮ እየቦካና እየበሰለ ከዚህ የደረሰውን ኢትዮጵያዊውን ስነ ልቡና ከዘመኑ ጋራ አገናዝበው የተነሱ ጋዜጠኞች ባለመፈጠራቸው የቅኔያችን መዋቅር እየተጠቀመ በቤተ ክህነቱ ዙሪያ ተዛብቶ የሚታየውን ስህተት የሚነካው ጠፋ። "መንግስት በህዝብ ላይ የሚፈጽመውን ደባ ማጋለጥ የካህናት ስራ አይደለም። የመንግስትን ስህተት የጳጳሳቱን ስህተት የሚናገር ሁሉ ፖለቲከኛ ነው" እያሉ የቤተ ክርስቲያናችንን አፍ እንደ ዘጉ ሁሉ፤ በጽጽስና በምንኩስናና በቅስና ራሳቸውን ደብቀው ስለሚሳሳቱ ሰዎች መናገርም ሃይማኖቱን መዳፈር ነው" የሚሉ ጋዜጠኞችም ገጥመውኛል።

ይሁን እንጅ በቤ ተክርስቲያናችን ግምጃ ቤት ያሉት በየእለቱ የምንጠቀምባቸው የጸሎት መጻሕፍቶቻችን እንደ ቅዳሴያችንና ኪዳናችን የመሳሰሉትን ሁሉ በመጠቀም፤ ሁሉንም ማለትም ነገረ ዘርቅ ቅኔ አቅራቢወችን፤ በነገረ ዝርቅ ተወዳሾችንና አገር አስወራሪዎችን ሊቃውንቱ በየዘመናቸው መገሰጻቸውን አላቆሙም። (*ከዚህ ቀደም በሀዳር ወር ፳፻፬ ዓ.ም "ኃያላን ይጽሕፉ ጽድቀ" በሚል ርእስ ያቀረብኩትን ጦማር ይመልከቱ።* http://medhanialemeotcks.org/wordpress/wp-content/uploads/2012/01/Hayalan-Final.pdf )::

በዘመናችን በህዝብ፤ በአገርና በቤተ ክርስቲያን ላይ መንግስት የሚፈጽመውን ደባ ማንም እንዳይናገር፤ የሚናገር ካለ ደግሞ ፖለቲካ ገባ እያሉ በማስፈራራት ያዘጋጇቸውን ሽፍጠኞች በሊቃውንቱ ላይ በማዝመት ቤተ ክርስቲያናችንን ከህዝብ፤ ከቅኔዋና ከመጻህፍቶቿ ለዩዋት። ይህም ብቻ አይደለም። ባላገሩ በየወቅቱ በበዓላትና በሰርግ ላይ የሚያከናውናቸው ባህላውያን ዘፈኖች የሚደመደሙት፤ ወንድነትን ጀግንነትን በሚያንጸባርቁ ለወድነት ወኔ ምንጮች እንደ ቅራርቶ (ሽለላ) ና ፉከራዎች ነበሩ። ይህ ሁሉ ተረስቶ፤ የወንድነት ወኔ ተሰልቦ እንዲቀር፤ ወደፊትም ተቀናቃኝ ወንድ እንዳይኖር ተደረገ። (ከዚህ ቀደም የነ ፋሌቅ ወጥመድ በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ይመልከቱ (ከዚህ ቀደም የነ ፋሌቅ ወጥመድ በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ይመልከቱ http://www.ethiomedia.com/2012_report/yene_faleq_wetmed.pdf)::

በክህነቱ ተሸፍነው ሥጋዊ ፈቃዳቸውን ለመፈጸም ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡ፤ ከሞራል_ቢስና፤ እምነተ_ጎደሎ መሪ ተጥግተው የሚኖሩ፤ ክርስትና ሳይገባቸው የሚመጻደቁ፤ የግለሰብ ኃጢአት ለምን ይጻፋል? በማለት በቤተ ክርስቲያናችንና ባገራችን ላይ የተዘረጋውን የረቀቀ የሞራል ሰለባ የሚያስተጋቡ ጳጳሳት፡ ካህናት በተለይም መንነናል የሚሉ የከተማ መነኮሳት በብዛት ተለቀቁብን። (ከዚህ ቀደም የዘመናችን መነኮሳት በዮሐንስ አፈወርቅ እይታ በሚል የተዘጋጀውን ጦማር ይመልከቱ http://medhanialemeotcks.org/wp-content/uploads/2011/01/yezare_sinodos.pdf)

መጽሐፍ ቅዱስ የዓቤልን ደግነት ሲመዘግብ፡ የቃኤልን ነፍሰ ገዳይነት አልደበቀም። የዳዊትን መጸጸት ሲገልጽ፤ ዝሙተኛነቱንና ነፍሰ ገዳይነቱን ሳይገልጽ አላለፈውም። የጴጥሮስንም ተጸጽቶ መመለስ ሲመዘግብ፤ ሶስት ጊዜ መካዱን አልዘለለውም።

ካህናት በተለይም ጳጳሳት ለህዝቡ በሞራል በሃይማኖትና በስነ ምግባር ምሳሌ ልንሆን ሲገባን እንዲያውም ህብረተ ሰቡ የሚያፍርብን በመሆናችን፤ ከህብረተ ሰቡ ፊት ዘወር ብለን እየተማርን ንስሀ እንድንገባ በቃልም በጽሁፍም የሚናገሩትንና የሚጽፉትን ሰዎች ኃጢአተኞች አርገን ለማቅረብ መሞከራችን ያለንበትን ዘመን ከመቸውም ክፉ ዘመን እጅግ የከፋ አደረገው።

በጆሯቸው ሰምተው በአይናቸው አይተው ለመመስከር የሚጽፉትን ሰዎች ባናውቃቸውም፤ ሞራልና ስነ ምግባር <u>በጎደላቸው ሰዎች ላይ የሚያቀርቧቸው ስህተቶች በማስረጃ ከተረጋገጡ፤ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ጥንቃቄ ሲባል ምስክርነታቸው ሊወድቅ አይገባም</u>።

ቅዱስ ጳውሎስ "እስመ ቀትልክሙኢኮነ ምስለ ሥጋ ወደም ዘእንበለ ምስለ መኳንንተ ጽልመት ወአጋንንት እኩያን እለ መትህተ ሰማይ"(ኤፌ ፮:፲፪) እንዳለው፤ የምንቃወመው የሰይጣንን ስራ ሀሰትን ክህደትንና ማስመሰልን ማታለልን እንጅ ሰውን ስላይደለ፤ በተሳሳተ ነገረ መለኮትና ቀኖና ላይ ያሉ ሰዎች፤ ይታረሙ ገለል ይበሉ ብለው የሚያቀርቡትን ስህተት ላለማረም "እነሱስ ቢሆኑ እነ ማናቸው?" ብሎ ማለፉ፤ ከኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን መመሪያ ውጭ ነው።

ማንም ሰው ቅዱስ እንዳልሆነ እና፤ ቅዱስ መባል ያለበት አምላክ ብቻ እንደሆነ የታወቀ ቢሆንም፤ "ቅዱስ እግዚአብሄር፤ ቅዱስ ኃያል፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት" እያሉ የአምላካቸውን ቅድስና እያሰቡ እንደ አምላካቸው ቅዱስ ለመሆን በሚታገሉ ምእመናን ፊት ቆሞ "ቅዱስ" የሚለው መሪ ካህን በዝሙት፤ በስርቆት፤ በመዋሸትና በሃይማኖት ሕጸጽ የሚከሰስ መሆን የለበትም። ከምእመናን ያነሰ ሞራል ያለው ሰው መምራት ይቅርና ክርስቶስ እንዳለው፤ ክርስቲያኖች "ከታናናሾች አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር"(ማቴ ፲፰:፮) ሊሉት ይገባል። ለብጽዕና፤ ለቅድስና እና ለቅስና ምሳሌነት በቅቶ ያልተገኘ ግለ ሰብእ ከምእመናኑ ባነሰ ግብሩ ቅዱስ ለማለት ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚመጡት ሰዎች እንቅፋት ከመሆነ መወገድ አለበት።

ቅዱስ ጳውሎስም "አሰምእ ለከ በቅድመ እግዚአብሔር ወኢየሱስ ክርስቶስ ወመላእክትሁ ኅሩያን ከመ ትዕቀብ ዘንተ እንዘ ኢታደሉ። ወኢታጽድቆ ለሰብዕ ቅድመ ፍትሕ። ወኢትግበር ምንተኒ በአድልዎ። ወኢትሳተፍ በኃጢአተ ባእድ ወአንጽህ ርእሰከ ፩ኛ ጢሞ ፭:፳፩) ማለትም፦ "የህሊናህን ፍርድ በማዛባት ለሰው አዳልተህ ከተሳሳተው ሰው ጋራ እንዳትወግን፤ የተሳሳተውን ሰው በመሸፈን እንዳትጋርድ። ይህን በማድረግም የበደል ተሳታፊ እንዳትሆን በእግዚአብሄርና በመልእክተኞቹ ታዛቢነት ፊት በአጽንኦት ነገር አረጋግጬ እነግርሀለሁ" እንዳለው፡ ከሳሹ ጻድቅም ይሁን ኃጢአተኛም ይሁን ያቀረበው ክስ እውነት መሆንና አለመሆን ለይቶ በማወቅ የተቀደሰውን የአምልኮ መቅደስና አውደ ምህረት ብቃት የጎደላቸውን ሰዎች እንዳይጠቀሙበት ለመጠበቅ በተቻለ መጠን መታገል እንጅ፤ <u>የተከሳሾችን ኃጢአት ከከሳሾች ኃጢአት ጋራ አቻችሎና ሁሉንም ታዝቦ ማለፍ፤ በህብረተ ሰብ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት የከበደ ይሆናል። ይህንን ለመረዳት ያለንበትን ሁኔታ ማስተዋል ይበቃል</u>።

በነዚህ ሁሉ መመሪያዎች እየተረዳን ችግሩን፤ የችግር ፈጣሪዎችንና ራሳቸው ችግር እንዳለ የሚናገሩትም የሚፈጥሩትን ችግር እንዳንልፈው እንዳንዘለው እውነቱን እየደገፍን ሀሰትን እየተቃወመን እንድንኖር ያዕቆብም "ዲያብሎስን ተቃወሙ" (ያዕ. ፬-፯) በማለት ተናግሯል። ቅዱስ ጳውሎስ "እንደ ጥበበኞች እንጅ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንደምትኖሩ በጥንቃቄ ተጠበቁ" (ኤፌ ፭:፲፭) ያለው ራሳችንን <u>ህብረተ ሰባችንና ቤተ ክርስቲያናችንን ከሀሰተኞች ካስመሳዮች እንድንጠብቅ እንጅ እኔ ምናገባኝ እግዚአብሄር ይፍረድበት ብለን ተስማምተን እንድንኖር አይደለም</u>።

ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖችም ቅዱስ ጳውሎስ "ትንቢትን አትናቁ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ ከማናቸውም ክፉ ነገር ራቁ" (፩ኛ ተሰ. ፭:፲፱-፳፪)። ብሎ የሰጣቸው መመሪያ፤ በእውነት ላይ ተመስርቶ የቀረበልንን ምስክርነት ንቀን እንዳንተው። <u>እየመረመርን ክፋውንና ሀሰቱን አውጥተ በመጣል፡ እውነቱን በመቀበል እንድንኖር እንጅ "እግዚአብሄር ይፍረ ድበት እኔ ምናገባኝ" ብለን እንድናልፈው አይደለም</u>። "እግዚአብሄር ይፍረድባቸው" ብለን እንድናልፋቸው የታዘዝነው፤ <u>በሃይማኖትና በባህል ከኛ የተለዩ ሰዎች በመካከላችን ሰርገው ሳይገቡ፤ በራሳቸው ክልል ተወስነው የሚያደርጉት ስራና የሚያካሄዱት አምልኮት ከኛ በመለየቱ ስህተት መስሎ በሚታየን ባህላቸውና አምልኮታቸው ያሉትን ሰዎች ብቻ ነው</u>። (፩ኛ ቆሮ. ፭:፲፫)

ነገር ግን ቀድሰን እናቁርባችሁ እንናዛችሁ እንባርካችሁ እያሉ የሚያታልሉትን ክርስቲያኖች እንዲያወግዟው እንዲያሳፍሯቸውና እንዲሸሿቸው "መለያየትን ከሚያነሳ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ ደጋግመህ ከገሰጽክ በኋላ ሸሸው" (ቲቶ ፫፥፲፩) በማለት ቅዱስ ጳውሎስ አዝዟል።

ሊቃውንትም "ዘበ ጽድቅ ትከውን ስምዐ መጽሀፈ ብሊት እንተ ይእቲ ትእዛዝ ቅድስት ቃለ እግዚ ወትርጓሜሆሙ ለአበዊነ ቅዱሳን እለ ረከብነ በኀቤሆሙ ኩነኔሆሙ ለዐላውያን እለ ዘከርኖሙ ቀዲሙ (ሃ ፶፪፥፳፬)በማለት፦ ማለትም ስህተት ሲሰሩ የተገኙ ሰዎች በቅዱሳት መጻህፍት እየተለኩ ምሳሌነት ከሚጠይቁ ቦታዎች እንዲወገዱ ለክርስቲያኖች አስተምረዋል።

"ኢትጻኡ እምቃለ መጽሀፍት ከመ ኢትትዐበዩ ላዕለ ቢጽክሙ"( ፩ኛ ቆሮ ፬፥፯) "ከተጻፈው አትለፉ" ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ በተናገረው መሰረት፤ ክርስቲያኖች በከንቱ (ያለ በቂ ምክንያት) የሰውን ስም ለማጥፋት የሀሰት ክስና ወቀሳ መፍጠር፤ ከሚፈጥሩት ጋራ መተባበር የለባቸውም። እንዲያውም ፈጣሪወችን ሊቃወሙ ይገባል። በተቃራኒው ደግሞ የሚደረገውን ክፉ ነገር ለሚደረገው ተቃውሞ እንቅፋት ሊሆኑ ይቅርና መሪወች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ክርስቲያኖች የሚያመሰግኑባቸው፡ የሚወቅሱባቸውና የሚከሱባቸው ነገሮች ሁሉ በብሉያቱ በሀዲሳቱና በሊቃውንቱ መለካት ይገባቸዋል። ከመጻህፍት ልክና መስፈርት ከተወጣ ስርዮት በሌለው በደል ተጠያቂነትን ያስከትላል።

<u>መስሎ የገባውን አሳሳች ሽፍጠኛውን ንስሀ እንዲገባ መምከር መገሰጽና በምሳሌነት ትውልድ እንዳይበክል ለይቶ ማውጣ እንጅ "እኛ ምን አገባን እግዚአብሔር ይፍረድበት ብሎ ዝም ብሎ ማለፍ መሸፋፈን ፈጽሞ ተገቢ አይለም። ለማስረጃ ከብሉያቱ ከሀዲሳቱ ከሊቃውንቱና ከመመሪያችንም ጥቂቶችን ከዚህ በታች ተመልከቱ</u>።

# <u>ከብሉይ ኪዳን</u>

**ሀ.** <u>አስመስለው ስለገቡ ሰዎች</u> "ወይቤ ሙሴ በዝንቱ ተአምሩ ከመ እግዚአብሄር ፈነወኒ ከመ እግበር ዘንተ ኵሎ ግብረ ከመ አኮ እምልብየ። ከመ ኢይሙቱ ከመ ሞተ ሰብእ ወከመ ኢኮነ መቅሰፍቶሙ ከመመቅሰፍተ ሰብእ"(ዘኍ ፲፯፥፳፭_፴፫)። ሲል ሙሴ ተናገረ። "በደለኛ በተገቢው የሞት ህግ ተፈርዶበት በሚሞትበት ሞት እንዳትሞቱ፤ ይሁን እንጅ በሰው ላይ ተደርጎ ባልታወቀ ከባድ መቅሰፍት እንድትሞቱ ለማድረግ ከልቤ አስቤው አይደለም። ነገር ግን ካህናት ሳትሆኑ መስላችሁና ተዳፍራችሁ በመግባታችሁ ይህ የሞት ቅጣት እንዲፈጸምባችሁ እግዚአብሄር ላከኝ" አለ። የሙሴ ንግግር፤ ቅዱስ ጴጥሮስ <u>"ፍርድ ከእግዚአብሄር ቤት ተነስቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሷልና አስቀድሞ በኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሄር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሳቸው ምን ይሆን? (፩ኛ ጴ ፬፥፲፯)</u> ሲል ከተናገረው ፍርድ የበለጠ አስፈሪ ፍርድ ነው።

**ለ.** <u>ሲዘሙቱ የተገኙትንም</u> "ወረገዘሙ ልክሌሆሙ ለውእቱ ብእሲ መንገለ ሀቋዌሁ ወለይእቲ ብእሲት እንተ መንገለ ሀፍረታ፡ ወሀደገ መቅሰፍት እምእስራኤል ወእግዚአብሄርኒ ነበቦ ለሙሴ እስመ ቀንአ ሊተ ቅንአትየ ላዕሌሆሙ ከመ ኢያጥፋእክዎሙ ለደቂቀ እስራኤል በቅንአትየ ወከመዝ እቤ ናሁ አነ እሁቦሙ ሕገ ሰላም"( ዘኍ ፳፭፥ ፰_፲፪) ማለትም፤ ሲዘሙቱ የተገኙትን ወጋቸው። እግዚአብሄርም ደስ አለው ተቀበለው። የዝሙት መንፈስ በዚ መንገድ በመገሰጹ እግዚአብሄር የመረጋጋትና የሰላም መመሪያ ሰጣቸው" ይህ መመሪያ "ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋው ውጭ ነው። ዝሙትን የሚሰራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይቀርጻል"(፩ኛ ቆሮ ፮፥፲፰) ተብሎ በተነገረው የበለጠ ተጠናክሯል።

# ከሐዲስ ኪዳን

ሰው መግደልና መደብደብ ይቅርና መስደብ በክርስትና ክልክል ነው። ይሁን እንጅ ሲዘሙቱ ሲሰርቁ ሲዋሹ የተገኙትን በተቀደሰው አውደ ምህረት ላይ ቆመው ካህናት መስለው ለማስተማርና ለማቁረብ ደፍረው የሚመጡትን መቀበል ይቅርና፤ በየመንደሩና በየ አደባባዩ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በዚህ ባህርያቸው የሚያውኩትን ለይታችሁ አስወጡ የሚል እንጅ፤ ተቀበሉ አቅፋችሁ ያዙ የሚል መጽሐፍ የለም።

- ፩ኛ አስመስለው የገቡትን ሰዎች ከመካከላችሁ ወንድሜ ካለቦታህ እዚህ ም ንተሰራለህ? ብለን እንድናስወጣው "እፎ ቦእከ ካልዕየ ዘኢለበስከ ልብሰ መር"፡ ብላችሁ እጅ ግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት" (ማቴ. ፳፪፡፲፩-፲፬) ብሎ ክርስቶስ አዘዘ።

- ፪ኛ ቅዱስ ጴጥሮስም "ይህን የመሰለ ሀሰት ነገርለምን በልብህ አሰብክ? እግዚአብሄርን እንጅ ሰውን አልዋሸህም(የሐዋ ፭፡፬)" በሚለው ንግግሩ ሸፍጠኞችን ከቤተ ክርስቲያን ላንድና ለመጨረሻ ጊዜ ለያቸው።
- ፫ኛ ቅዱስ ጳውሎስም፦ በውጭ ባሉት ሰዎች ከመፍረድ ይልቅ ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡ"(፩ኛ ቆሮ ፭፡፲፫) ብሎ ክርስቲያኖችን አዘዘ።

ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ ክርስቶስን እንደመሰልኩ እኔን ምሰሉ" እያለ ያስተማረው። "አትስረቅ ብለህ የምትሰብክ ራስህ ትሰርቃለህ፤ አታመንዝር የምትል እራስህ ታመነዝራለህ። መጀመሪያ እራስህን አታስተምር" (ሮሜ ፪፡ ፳፩) እያለ የጻፈውን መሰረዝ አንችልም። ይህ የተጻፈው እየሰረቁ እየዘሞቱ እየዋሹ ካህናት ነን የሚሉትን ሰዎች ኸረ እናንተ እነማናችሁ? ብለን እንድናሳፍራቸው እንጅ "እኛ ምናገባን እግዚአብሄር ይቅጣቸው" ብለን ሸፋፍንን እንድናልፋቸው አይደለም።

# ከሊቃውንቱ

- ሀ. አትናቴዎስ "ስቅል ውስተ ክሣውዲሁ ኃጋ ዘእሳት ወቦቱ ይስሀብ ውስተ ዐቢይ ሰቅል"( አ. ገጽ ፪፻፴፭ ቁ. ፻፴፯) ሲል፤ በዝሙተኞች ሰራቂዎችና ያለ አቅማቸው ወደ መንፈሳዊው አገልግሎት ገብተው ህዝብ የሚያሳስቱትን በውግዘት ሰንሰለት ታስረው ከህዝቡ መካከል እየተጎተቱ እንዲወጡ አስተማረ።
- ለ. ፍትሀ ነገስቱም "ይትነስኡ ላዕሌሁ በጽድቅ ወኢይህድግዎ ይትአደው ኀበ አባግዐ ክርስቶስ ዘተሣየጠሙ በደሙ"(ፍ. አ. ፭ ቁ ፻፹፭) ማለትም፦ ማንም ግለሰብ በክርስቶስ ክቡር ደም የተዋጁትን ሰዎች በየቦታው እየዞሩ በሀሰት በክህደት የሚያመሳቅሉትን ሰዎች አይታችሁ አትለፏቸው፤" ከቤተ ክርስቲያን አስወጧቸው" ብሎ መመሪያ ሰጠ።
- ሐ. ፍትሀ ነገስት ቀጠለና "እመቦ ዘይቶሉ ኖላዌ እኩየ ሞቱ ክሱት በቅድሜሁ"(ፍ. አ ፭፡ቁ ፻፵፱) ማለትም፦ "መሪው የተሳሳተ መሆኑን እያወቀ፤ ሳይቃወም ዝም የሚል ክርስቲያን እንደ ነፍሰ ገዳዩ እንደ ቃኤል ወንድሙን በሞት ለመሸኘትና ራሱንም ኮበላይና ተቅበዝባዥ ለማድረግ የወሰነ ኃጢአተኛ ሰው ነው" አለ።

እኛ ክህናቱ ከላይ የተገለጹትን መመሪያችንን በግልጽ ከማስተማር ይልቅ ክርስቶስ "ፈሪሳውያን ያዘዟችሁን ሁሉ አድርጉ ። ጠብቁትም። ነገረ ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ስራቸው አታድርጉ" (ማቴ ፳፫፡፫) ብሏል፤ እያልን የክርስቶስ ቃል አጣመን በመተርጎም፤ "የምናደርገውን ስህተታችንን ማየት

ኃጢአት ነውና አይናችሁን ጨፍኑ፤ በኛ ላይ ስለሚነገረው ኃጢአትም ከመስማትም ጆሯችሁን ድፈኑ" እያልን የምንሰብክ የሌባ ልብ አድርቆች ካህናት ቁጥራችን በዛ።

ፈሪሳውያን እኮ ክርስቶስን አምነናል ብለውና መስለው ወደ ክርስትና አልገቡም። ክርስቶስ ሕጉን በማነብነብ ለሚናገሩት ቃል በመጠንቀቅ የሚናገሩትን ስሙ አለ እንጂ፤መስላችሁ ኑሩ አላለም። ይልቁንም አምልኮቱን በባህል ጠቅለው ማታልያ ስላደረጉት ከእርሿቸው ሽሹ አለ እንጅ፤ በስሙ ተጠምቆ ከገባ በኋላ፤ ሃይማኖቱን ክዶ መጽሀፍ እያሳተመ በማሰራጨትና በአውደ ምህረት ላይ ቆሞ በክህደቱ የህዝቡን አዕምሮ ሲበክልና እምነቱን ሲያቃውስ እግዚአብሔር ይፍረድበት እኔ ምናገባኝ በማለት ልቀቀው ብሎ ክርስቶ ስ አላዘዘም። እንዲህ የሚል በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሀፋችን ተጽፎ የተቀመጠ ትእዛዝ ባንዲት ቦታ የለም።

<u>በስህተታቸው እንዲያፍሩ; ወደፊትም እንዳይቀጥሉ ቅዱሳት መጻህፍት በሚፈቅዱት መንገድ መገሰጽ መውቀስና መክሰስ የሃይማኖት የሞራልና የስነ ምግባር ግዴታ ነው።</u> እነዚህን በመሳሰሉ አጥፊወች ላይ የሚቀርበውን የሞራል የእምነትና የስነ ምግባር ምስክርነት በመቃወም "የሰውን በደልና ስህተት መናገርና መጻፍ ኃጢአት ነው" የሚሉ ሰዎች በሁለት አቅጣጫወች የተበደሉ መሆናቸውን መረዳት ያለባቸው ይመስለኛል።

፩ኛ ብንዘሙትም፤ ብንሰርቅም፤ ሀሰት ብንናገርም ካህናት ስለሆን "እግዚአብሄር ይፍረድባቸው በሉ እንጅ፡ አየነው ሰማነው ብላችሁ አትናገሩ፤ አትመስክሩብን እያሉ አስመስለው በገቡ ደፍተሮች ትምህርና ስብከት በመታሰር ተጎድተዋል።

፪ኛ ክህነቱን ሽፋን አርገው የፈለጉትን ሥጋዊ ስሜት ለመፈጸም ካህናትና ጳጳሳት እየመሰሉ ከገቡ ደፍተሮች ጋራ የጥቅም ተካፋዮች ሆነዋል። አንዱ ሌባ፤ ሌላውን ሌባ፤ ሌባ ነህ ብሎ መመስከር እንዳማይችል የታወቀ ነገር ነው። ክርስቶስም ሁሉም መሳዩን እንደሚደግፍ ነግሮናል። በትክክል ማስረጃ ተደግፎ የቀረበውን ምስክርነት ከመደገፍ ይልቅ ሃጢአትና በደል ነው በማለት የቀረበውን የሚቃወሙ ሰዎች እራሳቸው በደለኞችና ኃጢአተኞች መሆናቸውን መረዳት አለባቸው።

# <u>መደምደሚያ</u>

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን አባላት ላስገነዝበው የምወደው፤ ይህን ሳቀርብ እኔ ቅዱስ ነኝ በማለት አደለም። ወይም ባማንም ግለ ሰብ ላይ የተለየ ጥላቻ ኖሮኝ ጥላቻየን ለመወጣት አይደለም። ጳጳሳቱን ፓትርኩን ሰወቅስ እኔ ጳጳስ ወይም ፓትርያርክ መሆን አልችልምና፤ የነሱን ቦታና ክብር ለመሻማትም አይደለም። ለቦታው ቅድስናና ለተልእኮው ምሳሌነት ተጠንቅቀን፤ የተቀደሰውን ኦርቶዶክሳዊ ነገረ መለኮትና ስነ ባህርይ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማቀበል እንድንችል። በምድር ያለውን ተልእኳችንንም ፈጽመን፤ ተዘጋጅቶ ለሚጠብቀን ለሰማያዊው መንግስት የበቃን እንድንሆን ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ "ዘይትአመን ርእሶ ከመ ይቁም፤ ውእቱ ለይትዐቀብ ኢይደቅ"(፩ኛ ቆሮ ፲፡፲፪) ያለውን ባለመዘንጋት፤ ነፍሴ በማነኛውም አይነት ወጥመድ ተጠልፎ በሚወድቅ ሥጋየ ውስጥ እንዳለች አውቃለሁ። ነገር ግን <u>"ቅዱስ እግዚአብሄር፤ ቅዱ ኃያል፤ ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት" እያሉ የአምላካቸውን ቅድስና እያሰቡ፤ እንደ አምላካቸው ቅዱስ ለመሆን በሚታገሉ ምእመናን ፊት ቆሜ "ቅዱስ" ብየ የአምልኮቱን ስርአት ለመምራት ለህሊናየና ለምእመናን እንቅፋት የሚሆን ነገር እንዳልፈጽም ለመጠንቀቅ እሞክራለሁ።</u>

ህሊናየ ረስቶ በንስሀ ላልከፈልኩትና ልሸከመው ካቅሜ በላይ ለሆነብኝ ፍዳ (ክፍያ) የነስሀ በር ለከፈተልኝ ክርስቶስ እየተውኩ፤ "ወእመሰ እለ ንፌቅድ ንጸደቅ በክርስቶስ ኮነ ከመ ኃጥአን።ክርስቶስ ላእከ ኃጢአትኑ እንጋ። ሐሰ። እመሰኬ ዝኩ ኪያሁ ከመ አሐንጽ ዐላዌ ረሰይኩ ርዕሰየ"( ገላ ፪፥፲፯) እንዳለው፤ ማለትም፦ "ክርስቶስ በፈጸመው መለኮታዊና ሰባዊ ውህደት ድህነት ጸደኩ፤ዳንኩ ካልኩ በኋላ፤ እሱ የማይወደውን ነገር ብሰራ፤ እይጠቀመኝም ብየ የሸሸሁትን እንደገና የምከተል ከሀዲ ነኝ። ክርስቶስንም የኃጢአት አገልጋይ አደረኩት። አዋረድ ኩት" እንዳለው፤ በተዋህዶ አድኖኛል ብየ አምኜ አፍቅሬና አክብሬ የተከተልኩትን ክርስቶስ የማይወደውን ስራ እየሰራሁ ያማልደኛል በማለት እንዳላዋርደው እጠነቀቃለሁ።

እየዋሸ እየሸፈጠ እየሰረቀ እንተባበር የሚለኝን "እንብየ በልዎ ለጋኔን ወይጎይይ እምኔክሙ"(ያዕ ፬፥ ፯) "የሀሰት ምንጭ የሆነው ሰይጣን ከናንተ እንዲሸሸ ለሀሰት መንፈስ አትታዘዙ። ሀሰትን እምቢ፡ አንቀበልም በሉ" ሲል ቅዱስ ያዕቆብ የተናገረውን ለመፈጸም ከስህተት ጋራ ከመተባበር እጠነቀቃለሁ።

ይልቁንም "አርህቅ እግዚኦ ኩሎ ቅንአተ፤ ወኩሎ መከራ፤ ወኩሎ ግብረ ሰይጣን፤ ወምክረ ሰብእ እኩያን፤ ወትንሳኤ ጸር፤ ዘህቡእ ወዘገሀድ እምኔየ፤ ወእምነ ኩሉ ሕዝብከ ወእምዝንቱ ቅዱስ መካን" ( ሥ ቅ ገጽ ፴፪፥ ፴፯-፴፱) ማለትም፦አቤቱ አምላኬ በሰይጣናዊ ቅናት ተገፍተው። በሰይጣናዊ ተግባር ተመካክረውና አድመው በገሀድና በስውር የሚንቀሳቀሱትን ክፉ ሰዎች ከእኔም ከንጹሀን ክርስቲያኖችንና ከየቆምንበት ቅዱስ አውደ ምህረት አርቅልን ብየ እጸልያለሁ።

በመጽሀፈ ቅዳሴያችን "ክርስቶስ አምላክነ ረሰየነ ድልዋነ ከመ ንትአማኅ በበይናቲነ በአምኀ ቅድሳት" አምላካችን ክርስቶስ እርስ በእርሳችን እጅ ለመነሳሳት የበቃን አድርገን" እጅ መነሳሳት አገጭን ደረት ማስነካት አይደለም። ፍቅርና ርህራሄ በተመላው ተግሳጻችሁ ከወደኩበት የኃጢአት ጉድጓድ አውጡኝ ለንስሀም አብቁኝ ማለት ነው። ከዚህ ኦርቶዶክሳዊው ነገረ መለኮትና ስርአተ አምልኮት ጋራ ስለሚጋጭ፤ "ስሳሳት አትዩኝ። እግዚአብሄር ይቅጣኝ" ብየ አላስተምርም። የሚያስተምሩትንም እቃወማለሁ።

ይልቁንም ስርአተ አምልኮታችን "እመቦ ዘወድቀ በኃጢአት ኢይርሳዕ እስመ ዘኢይትረሳዕ" (ቅ እ ገ ፻፳፰፥፯) "መረሳት የለበትምና፤ በስህተት የወደቀ ካለ ስህተቱን አይርሳ" በሚል ኃይለ ቃል እኩል ካህኑ ምእመኑም ያስጠነቅቃል። ሊቃውንት ሲያብራሩትም "አንድ ሰው የመርሳት ችግር ኖሮበት በየሄደበት እቃ የሚረሳ ከሆነ መርሳቱን አይርሳ። በየደረሰበትና በያረፈበት ቦታ ሁሉ መርሳቱን ካስታወሰ የሚረሳውን አይረሳም" ይላሉ።

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስ ውስጥ; ክርስቲያኖች ለማገልገል የሚሰለፍ ካህን፤ በሁለት ታዛቢዎች መካከል እንዳለ መርሳት የለበትም። አንዱ ፈጣሪ ሲሆን ሁለተኛው ህዝብ ነው። ሰው የሚወድቀው በህቡዕ የሚመለከተውን የአምላክን ህልውና ሲክድና፤ ህዝቡ በገሀድ አይቶበት የሚያቀርብበትን ክስና ወቀሳ ንቆና ጥሶ ሲሄድ ነው። "ኢትፍቱ ወኢምንተኒ ዘተአምር ዘይከውነከ ቦቱ ሕጸጽ። አፍቅር ኩሎ ሰብአ ወይኩን ኩሎሙ ሰብእ በኀቤከ ክቡራነ ፈድፋደ እምርእስከ"(ሃ አ ፳፩፥፰) እንዳሉት ሰለስቱ ምዕት በህቡዕ የሚመከተውንና በገሀድ የሚያየውን ህዝብ የማይረሳ ካህን በሰውነቱ ድካም ቢኖረውም፤ በአውደ ምህረት ላይ በመቆም "ቅዱስ" ብሎ አምልኮቱን ለመምራት በራሱና በህዝቡ መካከል የህሊና መሰናክል አይፈጠርም" ብለው ሊቃውንት አበው የሚመክሩትን አስታውሳለሁ።

በበኩሌ መተርጉማን ሊቃውንት በራሳቸው ግንዛቤና ልምድ የሚሉትን ባለመዘንጋት፤ አብረውኝ ለሚኖሩት ክርስቲያኖች "ሰው ነኝ የምትታዘቡት ስህተት ካለብኝ፤ ስዋሽ፤ ስቀጥፍ፤ ስሰርቅና ወይም ቃሉን የጥቅም ማምረቻ ለማድረግ በቁልምጫ ወይም ለሥጋዊ ጥቅም መጋረጃ ለማድረግ አስመስየ ሳቀርብ ካያችሁብኝ ንገሩኝ" እላለሁ። ይህንን ባልል ሰው ነኝና እወድቃለሁ። ይህን እርዳታ እየጠየኩ፤ ለአምልኮታቸው እንቅፋት የሆነ ነገር ስፈጽም ባካባቢያ ያሉት ክርስቲያኖች እያዩብኝ ባይነግሩኝና

ሽፋፍነው አምልኮቱን ከኔ ጋራ ቢቀጥሉ፤ እያወኩ ለፈጸምኩት በደል ከተጠያቂነት ባላመልጥም፤ ሳላውቅ ለፈጸምኩት በደል ግን ተጠያቂዎቹ "እኛ ምን አገባን" በማለት ከኔ ጋራ አምልኮቱን የሚሳተፉ ክርስቲያኖች ናቸው።

በቤተ ክርስቲያናችን ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተሰለፍን ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችን በምታስተምረው ነገረ መለኮት የምትከተለውን መንፈሳዊነት ከለቀቅን፤ ቤተ ክርስቲያናችን የእምነት የሞራልና የስነ መግባር መለኪያነቷ ተሰርዞ በዝሙት በቅጥፈት በዘረፋ በሀሰት መኖሮ ትክክል መስሎ የሚታየቸውን ሰዎች እንዲያቆሙ ወደፊትም እዳይቀጥሉ ይረዳል ብየ ስላመንኩ ነው። አሁን ባለንበት ቀውስ ብንቀጥል ከኛ በኋላ የሚመጣውን ትውልድ እንደገደልነው ስለተሰማኝ ነው።

ከጥንት ጀምሮ የነበሩት ነብያት፤ ሐዋርያትና ሊቃውንት ከዚያም ወዲህ እስከ ቅርብ ድረስ እንደነበሩት እንደ ሊቀ ካህናት ወልደ ዮና በሀገር በቤተ ክርስቲያንና በህዝብ በደልና ኃጢአት ሲፈጸም በከንቱ ውዳሴ በዕለታዊ ጥቅም ሳይደለሉ ሀላፊነታቸውን እየተወጡ እንዳለፉት እኛም የነሱን ፈለግ መከተል አለብን። በነገረ መለኮታችን በቀኖናችንና በስርአት ምህርታችን እየተመራን ራሳችንን እያጸዳን ቤተ መቅደሱን ለማጽዳት እንሞክር። ይህን ማድረግ የምንችለው የተሳሳተውን ተሳስተሀል ያለቦታህ ገብተሀል ስንል ብቻ ነው።

በተፈጠረው መለያየት እርቅ ይደረግ እየተባለ ሳለ፤ ፓትርያርክ ለመሰየም እጩዎች ቀረቡ ተብሎ መነገሩ የሚያስገርም ነው። ቀድሞ በየመንደሩ ተደረጉ እየተባለ ሲነገሩ የሚሰሙት አሰቃቂ ስህተቶች በካህናት ያውም ደግሞ በጳጳሳት ተደረጉ እየተባለ በተለያዩ መገኛዎች በተለይም በራሱ በቤተ ክህነቱ ጋዜጣ ተደጋመው እየተገለጸ ናቸው። እነዚህ ስህተቶች እየተለመዱ፤ የባህል ውርስ ሆኖነው እንዳሽገሩ፤ ስህተተኞችም ከስህተታቸው እንዲገቱ ለማሳሰብ፤ የተዘጋጁትን ጦማሮች ከዚህ በመቀጠል ተራ በተራ አቀርባለሁ::

**ይቆየን!**

*ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::*

http://www.medhanialemeotcks.org/